# የዝቋላ ተራራ ትዝታ…2

ገ/ኢ. ጐርፉ።

የዝቋላን መልክዓ ምድር ስንመለከት በብዙ ክፍለ ዓለማት ያሉትን የእሳተ ገሞራ ተራሮችን፣ በተለይ በጃፓን አገር ያለውንና እጅግ የታወቀውን የፉጂ ተራራን ይመስላል። ቅርጹ በእሳተ ገሞራ ፍንዳታ የሚወጣ ቀለጠ ግንፋሎት ቀዝቅዞ፣ ወደ አፈርና ድንጋይ ተለውጦ የተራራው አካል ከመሆን የመጣ ነው። በዓለም ላይ ይኸ ቅርጽ ያላቸው ብዙ ተራሮች ቢኖሩም እንኳን፣ ከጫፋቸው ጉድጓዳ የውሃ ኩሬ ያሏቸው መኖራቸውን እንጃ፣ ይህ በዝቋላ ተራራ ብቻ የሚታይ ገጽታ ሳይሆን አይቀርም።

እራት ከበላን በኋላ የመኝታ ነገር ሲመጣ፣ ከቤተክስያኑ ጥግ ከገላጣ ሜዳ ላይ እንድንተኛ መሩን። ብርድ ልብስ ይዞ የመጣ ብርድ ልብሱን፣ ነጠላ የያዘ ነጠላውን፣ ካቦርት ያለው ካቦርቱን፣ ምንም የልያዘም ኮቱን ደርቦ፣ ለባብሶ፣ ከገላጣው መሬት ተጋደምን። በጋ ሰለነበር፣ ከተራራው ከፍታ መጠነኛ ቅዝቃዜ ቢኖርም፣ ተራራውን የሸፈነ ዳመናና ጉም እንደ ብርድ ልብስ ሆኖልን፣ እጅግም አልበረደንም። የመቆርቆሩ ነገር ግን አይነሳ! ቀን በተጓዝነው ጉዞ ሁላችንም ተዳክመን፣ ማለፍያ የሆነውን እራትም በልተን፣ ጠግበን፣ ሆዳችንም ስለ ተቆዘረ ብዙ ሳንቆይ እንቅልፍ ወሰደን።

ቢበዛ ከሦስትና ከአራት ሰዓት የሚበልጥ የተኛሁ አይመስለኝም፣ የመሬቱ ደረቅነትና የጠጠሩ መጎርበጥ ስላስቸገረኝ ከእንቅልፌ ነቃሁ። ፍራሽ የለመደ ጀርባ ከደረቅ መሬት በቀላሉ መች ይተኛል! ፊቴን ገለጥ ሳደርግ ምሽቱ ተራራውን ሸፍኖት የነበረው ዳመና የለም፣ ሄዷል። በቦታው ግን ደማቅ ጨረቃና ከዋክብት ወለል ብለው ይታያሉ። ታድያ የብርዱ ነገር አሁን መጣ፣ ቆማጣን የሚያሳቅፍም ሆነ። ማምለጫ ግን አላገኘንም።

በግምት ለግማሽ ሰዓት ያህል ከተጋደምኩበት እንደተገላበጥሁ፣ "እህህህ!" የሚል የችግር ድምፅ ሰማሁ። ብርዱና የመሬቱ ጎርባጣነት ያስመረረው መንገደኛ ጓደኛየ መሆኑን ገባኝ። ሌሎቹን ላለመቀስቀስ ድምፄን ዝቅ አድርጌ፣ "ነቅተሃል እንዴ?" ብዬ ስጠይቅ፣ ወድያው ሁሉም በአንድነት የተማከሩ ይመስል፣ "እንዴት መተኛት ይቻላል፣ ከመሬቱ መጎርበጥ፣ ከብርዱ… አረ ምኑ ቅጡ!" እያሉ ከዚህም ከዚያም ያማርሩ ጀመር።

ከቤተክስያኑ ጥግ ከነበረችው ጎጆ ብጤ የተኙት መነኩሴ እየቆዩ ሲስሉ ይሰማሉ። ከመሃከላችንም አንዱ የመረረው፤ "አባ! አረ ብርድ አለቅን! ምነው ከጎጆዎ ትንሽ ቦታም የለ?" ብሎ ተጣራ። ገና "በሉ ኑ፣ ግቡ…" ብለው በሩን ከፈት ማድረጋቸውን ስንሰማ ስድስት፣ ወይ ሰባት የሚሆኑ ተማሪዎች ግር ብለው ከጎጆው እየሮጡ ሄዱ፣ ግን ከሦስት፣ ወይ ከአራት

ሰዎች በላይ ቦታ ባለመኖሩ፣ ሌሎቹ እያማረሩ ፊት ከነበሩበት ገላጣ ሜዳ መጥተው ተጋደሙ። ጎጆው ውስጥ ከገቡትም ሁለት ተማሪዎች ብዙ ሳይቆዩ "አረ ተባዩ ፈጀን!" እያሉ፣ በቁንጫና በቅማሉ እያማረሩ፣ ጥለው፣ ከሜዳው ይሻለናል በማለት ተመልሰው መጡ።

በብርዱ ቆፈን፣ በተባዩ፣ በኮረኮንች መሬቱ እየተሰቃየን፣ እንዳይነጋ የለም ነጋ። የማለዳ ፀሓይ እንደዚያን ሌሊት አምራን፣ በጉጉትም ናፍቀንናትና ተመኝተናት የጠበቅንበት ጊዜ ኣላስታውስም። ብልጭ እንዳለች ሁላችንም እየሮጥን ፀሓይ ወዳለችበት ጉብታ አምርተን ልንሞቅ ተቀመጥን። የማለዳ ፀሓይ ለካ እንዲህ ይጥማል! ጦጣውና ጉሬዛውም እንደኛው በየቅርንጫፉ ፀሐይ ሲሞቁ እናይ ነበርን። እነሱንም ለካ ብርድ ሲፈጃቸው አድሯል። በፀሓይ ሙቀት ነፍስ ዘርተን ለመንሰራራትና ለመንጠራራትም ቻልን።

ፀሓይ ስንሞቅ ከቤተክስያኑ የጥዋት ቅዳሴ ሲካሄድ ኖሮ፣ ረፈድ እንዳለ ተፈጽሞ፣ የዘኬ መክፈልት ሆነ። እኛም ከዚያው ሄደን የዳቦ ቁርስ በላን። ከቤተክስያኑ ጐንም ወደ ኣፋፉ ጠጋ ብለን ስናይ ከኣይሮፕላን ላይ ያለን ይመስል የኣድኣና የከረዩ ሜዳ ወለል ብሎ ተዘርግቷል። ከበስተሰሜን የኣዲስ ኣበባ ከተማ፣ ከጀርባውም የእንጦጦ ተራራ፣ ትንሽ ቀረብ ብሎም ወደ ምስራቅ በኩል የየረር ተራራ፣ ወደ ደቡብ ምስራቅም የደብረ-ዘይት ከተማና በኣካባቢዋ ያሉ ባሕሮች፤ ሖራ፣ ጨለቅለቃ፣ ብሸፍቱ፣ ኩሪፍቱ፣ ወዘተ… ትንንሽ ጉድጓዶች መስለው ይታያሉ። እጅግ ደስ የሚል ነበር።

ኣንድ ሽማግሌ መነኩሴም፤ "ለመሆኑ የዚህ ገዳምን ታሪክ ታውቃላችሁ?" ሲሉ ቀረቡን። ኣናውቅም ስንላቸው፤ "ድሮ የሰይጣን ምሽግ ነበር። ኣባ ገብረ መንፈስ ቅዱስ ታድያ ቦታውን ሲያዩት ወደዱትና ወደ እግዚሃር ሄደው፤ 'ምነው ይህን ገነት የመሰለ ቦታ ለዲያብሎስ ሰጠኸው?' ኣሉት።

እግዚሃርም፤ 'እኔ መች ሰጠሁት፣ ራሱ ይዞት እንጂ!' ኣላቸው። ኣባ ገብረ መንፈስ ቅዱስም፣ 'በል ፍቀድልኝና ልቀማው?' ሲሉ ተማጠኑት። 'እሺ፣ ከቻልክማ ንጠቀውና ውሰዳ!' ኣላቸው። ኣባም ተነሱና ዲያብሎስን ጦርነት ገጠሙት። ይዘውም በመብረቅና በነጐድጓድ ሲሉት ጊዜ፣ ኣንድ እግሩን ቆረጡት። ሰይጣኑ ሲሸነፍ ታድያ፣ በእሳተ ነበልባል እየተፈጀ መሸሻውን ፈልጐ፣ በቀረችው እግሩ እንጣጥ ብሎ ዘሎ ባንድ እርምጃ ከሖራ ጥልቅ ብሎ ገባ። ትላንት ተዚያ ወድያ ያያችሁት የድንጋይ ክምርም የሰይጣኑ ቆራጣ እግር የተቀበረበት ነው።" ኣሉን። በጣም የሚደንቅ ጉድ ነው።

የሖራ ባሕር 'ቆሪጥ' የሚሉት ሰይጣን ኣለበት ተብሎ የሚወራውስ ለካ ለዚህ ኖሯል። ሁሉን ኣይተን፣ መነኩሳቱን ተሰናብተን፣ ወደ መጣንበት ልንሄድ ተነሳን። ከተራራው ለመውረድም ቁልቁለቱን ተያያዝነው።